## የኢነርጂ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች፣ ማናጀሮች እና የኢነርጂ ኦዲተሮች ፈቃድ አሰጣጥ ረቂቅ መመሪያ አጭር ማብራሪያ

### መግቢያ

የሃገሪቱን የኢነርጂ ተደራሽነት ለማረጋገጥ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን ማረጋገጥ አስፈላጊ እና ዋናዉ መንገድ በመሆኑ፤ለዉጤታማነቱም ብቃት ያላቸው የኢነርጂ ኦዲተሮች እንዲኖሩ ማገዝ እና መቆጣጠር ፣የኢነርጂ አገልግሎት አቅርቦት ገበያን ለማሳደግ እና የኢነርጂ ብቃትን በማሳደግ ብሔራዊ ጥረቱን መደገፍ፤ከታዳሽ የኢነርጂ ምንጭ የሚገኘን ኢነርጂ መጠን ማሳደግ፤የኢነርጂ ቁጠባ ልኬትና የማረጋገጥ ስራዎች እንዲከናወኑ ለማስቻል ይህንን መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ ፡-

የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 40(2) እና በደንብ ቁጥር 447/2011 አንቀፅ 82 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህ የኢነርጂ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች፣ማናጀሮች እና የኢነርጂ ኦዲተሮች ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

ይህ ረቂቅ መመሪያ ሲዘጋጅ ያደጉ አገሮችን በዘርፉ ያሉ የህግ ማዕቀፎችን በመመርመር፣የቁጥጥር ስራዉን በማሻሻል የዘርፉን ልማት እንዲያሳድግ ታስቧል፡፡ በዚሁ መሠረት ረቂቅ መመሪያዉ አምስት ክፍሎች እና 24 አንቀጾች ያሉት ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

1. ክፍል አንድ ከአንቀጽ 1 እስከ 4 የያዘ ሲሆን ፣
   - አንቀጽ 1 <u>አጭር ርዕስ</u> የመመሪያዉ ስያሜ “የኢነርጂ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች፣ማናጀሮች እና የኢነርጂ ኦዲተሮች ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ” በሚል ተሰይሟል፡፡
   - አንቀጽ 2 <u>ትርጓሜ</u> ላይ በኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 እና ደንብ ቁጥር 447/2011 ስር የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ተመላክቶ ትርጉም ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የታመነባቸዉ 17 ቃላት ተተርጉመዋል ፡፡
   - አንቀፅ 3 የመመሪያዉን ዓላማ በዝርዝር ያስቀምጣል፣
   - አንቀፅ 4 ስለ የተፈፃሚነት ወሰን መመሪያዉ በኢትዮጵያ ዉስጥ በሚሰሩ በኢነርጂ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች፣ማኔጀሮች እና በኢነርጂ ኦዲተሮች ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን ይደነግጋል ፡፡

2. ክፍል ሁለት ከአንቀጽ 5 እስከ 9 የያዘ ሲሆን ፣

- ስለ ኢነርጂ ኦዲተር ፈቃድ አሰጣጥና ማሟላት ስለሚገባቸዉ መስፈርቶች ፣
- ስለ ኢነርጂ ኦዲተሮች ተግባራቶች ፣
- ስለ ኢነርጂ ኦዲተር ፈቃድ አሰጣጥ የምዘና ሂደት ፣
- ስለ የኢነርጂ ኦዲተሮች የአፈፃፀም ምዘና
- ስለ የኢነርጂ ኦዲተር የስልጠና ፕሮግራሞች በዝርዝር ተቀምተዋል ።

3. ክፍል ሶስት ስለ ኢነርጂ ማናጀር ተግባራትና ፈቃድ ሆኖ ከአንቀፅ 10 —14 ያሉት ፡-

- ስለ ኢነርጂ ማናጀር ፈቃድ አሰጣጥና ማሟላት ስለሚገባቸዉ መስፈርቶች ፣
- ስለ ኢነርጂ ማናጀር ተግባራቶች ፣
- ስለ ኢነርጂ ማናጀር ፈቃድ አሰጣጥ የምዘና ሂደት ፣
- ስለ ኢነርጂ ማናጀር የአፈፃፀም ምዘና
- ስለ ኢነርጂ ማናጀር የስልጠና ፕሮግራሞች በዝርዝር ተደንግጓል ።

4. ክፍል አራት ስለ ኢነርጂ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያ ተግባራትና ፈቃድ ሆኖ ከአንቀፅ 15 - 20 ያሉት ፡-

- ስለ ኢነርጂ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች ፈቃድ አሰጣጥና የሚሸፍናቸው የስራ ዘርፎች ፣
- ስለ ኢነርጂ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች የፈቃድ መስጫ መስፈርቶች ፣
- ስለ ፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታዎች ፣
- ስለ ኢነርጂ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች ፈቃድ አሰጣጥ የምዘና ሂደት ፡
- ስለ አጠቃላይ የፈቃድ አሰጣጥ ምዘና መስፈርቶች፣የቴክኒክ ችሎታ ምዘና፣ሲስተም ( ስርዓት )እና መሣሪያዎችን ስለማደራጀት ፣ማመልከቻን ስለማቅረብ ፣ፈቃድን ስለመስጠት ተደንግጓል ፣

5. ክፍል አምስት ስለ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች የሚመለከት ሲሆን ከአንቀፅ 21 — 23 ያሉት ፡-

- ስለምስጢራዊነት ፣የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች እና መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ ይደነግጋል ።

በአጠቃላይ የረቂቅ መመሪያዉ አስፈላጊነት ታምኖበት በአዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 41 ሥር ያሉ ሂደቶችን ሁሉ በማሟላት ተዘጋጅቶ በባለሥልጣኑ ፀድቆ የቀረበ በመሆኑ ታይቶ እንዲመዘገብልን በድጋሚ ቀርቧል፡፡